Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

መመሪያ ቁጥር 36/2005

## ወደ ውጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጉማ መመሪያ

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን የ11 በመቶ አማካይ አመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ግብ ለማሳካት በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ከአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ቅርብስ ኤክስፖርት የሚገኘውን አመታዊ ገቢ ከ201.7 ሚሊዮን ወደ 1,483 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ የታቀደ በመሆኑ፣

በአዲስ መስመር ይህንን የሆልቲካልቸር ልማት ግብ ለማሳካት የገበያ፣ የሎጂስቲክና የትራንስፖርት ችግሮችን በመፍታት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ቅርብስ ምርት ውጤቶችን ከመቀሌና ባህር ዳር የማጓጓዣ ወጪ ከአዲስ አበባ የኤክስፖርት ማጓጓዣ ወጪ ጋር የሚመጣጠን ያለመሆኑ በሁለቱ ክልሎች አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ቅርብስ አምርተው ወደ ውጪ የሚልኩ ባለሀብቶች በውጪ ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖ የፈጠረ በመሆኑ፣

ይህንን ችግር በማቃለል በሁለቱ ክልሎች በሆርቲካልቸር ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶችን ለመደገፍ በአዲስ አበባ እና በሁለቱ ክልሎች መካከል የሚታየውን የሆርቲካልቸር ምርቶች የአየር ትራንስፖርት ታሪፍ ልዩነት በመደጉም የትራንስፖርት ወጪውን ተመሳሳይ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ወጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ወደ ውጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች የትራንስፖርት ወጪ ድጉማ መመሪያ ቁጥር 36/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ የሆርቲካልቸር ምርቶች ማለት የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ቅርብስ ምርቶች ማለት ነው።

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ የሆርቲካልቸር ምርቶችን ከመቀሌና ከባህር ዳር ኤርፖርቶች ለማጓጓዝ የሚጠየቀውን የትራንስፖርት ታሪፍ ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ማጓጓዣ ታሪፍ ጋር ተመሳሳይ ለማድረግ በሦስቱ የበረራ መስመሮች መካከል የሚታየውን የታሪፍ ልዩነት በመንግስትና በኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲሸፈን በማድረግ ኤክስፖርቱን መደገፍ ነው፡፡

## 4. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረግ የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ ተጠቃሚ የሚሆኑት በባህር ዳርና መቀሌ አካባቢዎች በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ተሰማርተው ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ የሚልኩ ድርጅቶች ብቻ ናቸው፡፡

## 5. የትራንስፖርት ወጪ መጋራት

1. የሆርቲካልቸር ምርቶችን ከመቀሌና ባህር ዳር ኤርፖርቶች የማጓጓዣ ሂሣብ ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ማጓጓዣ የአየር ትራንስፖርት ሂሣብ ጋር ተመሳሳይ ለማድረግ ከሚታየው የዋጋ ልዩነት 2/3ኛው በመንግስት 1/3ኛው በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

2. ከባህርዳር ወደአዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት የሚጓጓዘውን የአበባ ምርት ማጓጓዣ ወጪ ሙሉ በሙሉ መንግስት ይሸፍናል፡፡

## 6. ከዚህ መመሪያ አፈፃፀም ጋር ግንኙነት ያላቸው ተቋሞች የሥራ ድርሻ

### 6.1. የሆርቲካልቸር አምራቶች

ሀ. በኢትዮጵያ አየር መንገድ በሚያዝላቸው የበረራ ፕሮግራም መሠረት ማሟላት የሚገባቸውን ፎርማሊቲዎች/ ሰነዶች አዘጋጅተው ምርቶቻቸውን ለጭነት ማቅረብ አለባቸው፡፡

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

ለ. በአውሮፕላን ተጓጉዞ ወደ ውጭ ለተላከው ምርት ብቻ የድጎማ ክፍያ ይጠይቃሉ:: ለዚህም ተገቢውን ሰነድ ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ያቀርባሉ::

ሐ. አበባ አምርተው ወደ ውጭ ለመላክ ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት የሚያጓጉዙ ድርጅቶች ደግሞ ለማጓጓዣ ያወጡትን ወጪ የሚያረጋግጥ ሰነድ ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የሚያቀርቡ ይሆናል::

## 6.2. <u>የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ</u>

ሀ. በዚህ መመሪያ መሠረት ለየሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች ለሚደረገው የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የሚውል የበጀት ጥያቄ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል::

ለ. ወደውጭ የተላከውን የሆርቲካልቸር ምርት መጠን፣ በላኪዎች በመለየት የሰነድ መረጃዎች ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲሁም ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ አበባ አምራቾች አሰባስቦ ይይዛል:: የሰነዱንም ትክክለኛነት ያረጋግጣል::

ሐ. ባሰባሰበው መረጃ መሠረት የሚያስፈልገውን የድጎማ ገንዘብ እንዲለቀቅለት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጽሑፍ ጥያቄ ያቀርባል::

መ. የጠየቀው የድጎማ ገንዘብ ሲለቀቅለት የሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች ለውጪ ገበያ በላኩት ምርት መጠን ገንዘቡን ይከፍላል:: ለዚህም ተገቢውን የሂሣብ ሰነድ ይይዛል:: የክፍያ አፈፃፀም ሪፖርትም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ ያቀርባል::

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

## 6.3. የኢትዮጵያ አየር መንገድ

ሀ. የሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች በያዘው የበረራ ፕሮግራም መሠረት በቂ የጭነት አውሮፕላን ያቀርባል፡፡

ለ. ወደውጭ ያጓጓዘውን የሆርቲካልቸር ምርቶች መጠን እንዲሁም የላኪ ድርጅቶችን ስም የያዘ መረጃ ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ይሰጣል፣ የአፈፃፀም ሪፖርትም በየወሩ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

## 6.4. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች ወደ ውጭ የላኩትን የምርት አይነትና መጠን በየድርጅቶቹ በመለየት ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ያቀርባል፡፡

## 6.5. የትራንስፖርት ሚኒስቴር

በመመሪያው አፈፃፀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 6.6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

ሀ. ከኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ለሆርቲካልቸር ምርቶች የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የሚውል በጀት ይይዛል፡፡

ለ. የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የድጎማ ገንዘብ እንዲለቀቅለት በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ገንዘቡን ወደ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የባንክ ሂሣብ ያስተላልፋል፡፡

ሐ. የተለቀቀውን ገንዘብ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የራሱን ኢንስፔክተሮች ቡድን በማሰማራት የሂሣብ ምርመራ ያደርጋል፡፡ ስህተት ከተፈፀመም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል/ያስወስዳል፡፡

PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

7. **<u>የድጐማ ክፍያ የቆይታ ጊዜ</u>**

በዚህ መመሪያ መሠረት ለሆርቲካልቸር ምርቶች ኤክስፖርት የትራንስፖርት ወጪ ድጐማ የሚደረገው ለ2006 የበጀት አመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል፡፡

8. **<u>መመሪያው በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

*አዲስ አበባ ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ሚኒስትር*

Dir.Fol.Bo/GT